# የ2002ዓ.ም የግማሽ ዓመት እቅድ ክንውን ሪፖርት

## 1. መ ግ ቢ ያ

በዞኑ ውስጥ ፈጣን ልማት ለማምጣት መልካም አስተዳዳርን በማስፈን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚታዩትን የማስፈፀም አቅም ክፍተቶች ለይቶ በመሙላት ሕዝቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የተጀመረውን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR / ወደማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ማድረስ ቁልፍ ተግባር ተደርጐ ታቅዷል ፡፡

ከዚህ በመነሣት በአንደኛ ዙር ሆነ በሁለተኛው ዙር ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡ ሴክተሮችን ተከታትሎ የአፈፃፀም ክፍተቶችን በመለየት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጡ ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ከፍተኛ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል ፡፡

ስለዚህ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ፣ በመልካም አስተዳደር ፣በፍትህ ስርአት ማሻሻያና በምህንድስና አቅም ግንባታ እንዲሁም በሌሎች ተግባሮች የተሰጡ ድጋፎችና የተመዘገቡ ለውጦች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

## I. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም

መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በዞኑ በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ተግባራዊ በማድረግ በየደረጃው ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት ለማምጣትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል ፡፡ በዞናችን በአሥሩ ወረዳዎችና በቦንጋ ከተማ አስተዳደር የዞን ሴክተርን ጨምሮ በሁሉም ሴክተሮች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግበራ የገቡ ሲሆን ለውጡን ወደማይቀለበስበት ደረጃ ለማድረስ ባለፉት ስድስት ወራት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተደርጓል ፡፡

በዚህም መሠረት ከገዋታ ወረዳ በስተቀር በቼክ ሊስት የታገዘ ድጋፋዊ ክትትል የተደረገባቸውን ሴክተሮች ለመለየት ተችሏል ፡፡

በ2002 በጀት ዓመት በአንደኛው ግማሽ ዓመት በቂ ድጋፋዊ ክትትል የተደረገላቸው ሴክተሮችን የሚያሣይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ዞን/ወረዳ | ድጋፋ የተረገላቸው ሴክተሮች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ዞን ማዕከል | 16 |
| 2 | ጨና ወረዳ አቅም ግንባታ | 7 |
| 3 | ዴቻ ወረዳ አቅም ግንባታ | 15 |
| 4 | ጊምቦ ወረዳ አቅም ግንባታ | 4 |
| 5 | ቦንጋ ከተማ | 12 |
| 6 | አዲዮ ወረዳ አቅም ግንባታ | 14 |
| 7 | ጠሎ ወረዳ አቅም ግንባታ | 16 |
| 8 | ጨታ ወረዳ አቅም ግንባታ | 8 |
| 9 | ሣይለም ወረዳ አቅም ግንባታ | 15 |
| 10 | ጌሻ ወረዳ አቅም ግንባታ | 15 |
| 11 | ገዋታ ወረዳ አቅም ግንባታ | - |
| ድምር | | 122 |

መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ወደ ማይቀለበስበት ለማድረስ ተከታታይነት ያለው ድጋፋዊ ክትትል ከአቅም ግንባታ ሴክተር የሚጠበቅ ቁልፍ ተግባር ነው ፡፡

በዚህ መሠረት በቂ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ ወደፊት የወጡት አምስት ወረዳዎች ጠሎ፣ዴቻ፣ሣይለም ፣ጌሻና አዲዮ ሲሆኑ ከሰባት እስከ አሥራ ሁለት ሴክተሮችን በበቂ ሁኔታ በመደገፍ መሀል ላይ ቢጣ፣ጨና፣ጨታና የቦንጋ ከተማ አስተዳደር ይገኙበታል የጊምቦ ወረዳ የሰጠው ድጋፋዊ ክትትል እጅግ አነስተኛ ሲሆን የገዋታ ወረዳ ለሴክተሮች ድጋፋዊ ክትትል ለመስጠቱ ምንም መረጃ የለም ፡፡በድጋፋዊ ክትትሉ ወቅት በዞን ሴክተር መ/ቤቶች ቲም ቻርተር በመፈራረም የየዕለት ሥራን በመመዝገብና በመገምገም ሣምንታዊና ወራዊ አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለተገልጋይ በማሣወቅ የተገልጋዩች አስተያየት በመቀበልና  በማስተናገድ የንግድና ኢንዱስተሪ ሴክተር በአንፃራዊ መልኩ የተሻለ እንቅስቃሴ የሚታይበት ሲሆን የግ/ገ/ልማት ሴክተር ላይ ግን የሚጠበቀውን ያህል እንቅስቃሴ አይታይም፡፡ በወረዳዎች በተደረገው ምልከታ በአዲዮ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ የተሰራ ሥራ የአዲዮ ወረዳ አቅም ግንባታ ባለሙያዎች ዩኒፎርም ለብሰው አገልግሎት መስጠታቸው ለአብነት የሚጠቀሱ ለውጦች ናቸው ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ውጤቶች ባሻገር ትግባራው በአስተማማኝነት እንዲሰርጽ ለማድረግ ለዞን ሴክተር ሠራተኞች የግማሽ ቀን ኦረንተሺንና የልምድ ልውውጥ መድረክ የተዘጋጀ ሲሆን የሁሉንም ወረዳ አቅም ግንባታ ኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎችን ያሣተፈ አንደኛ ዙር የሴክተር ጉባኤ ተደርጐ አፈፃፀሞችን ለመገምገም ተችሏል ፡፡

## በመረጃ መሰብሰብና ማሰራጨት የስራ ሂደት የተከናወኑ

የመረጃ ተቀባዮችን ፍላጎት ከግምት ባስገባ መልኩ ተገቢ ፎርማት ተዘጋጅተው እስከ ሰኔ 30/2001 በዞን ማዕከላትና በየወረዳ የነበረው ጠቅላላ የመንግሥት ሠራተኛ ብዛት ስታትስቲካዊ መረጃ ተሰብስቦና ተጠናቀሮ ለባለድርሻ አካላት የተላለፈ ሲሆን ይህም የሚያሳየው ባጠቃላይ የ11ዱን ወረዳዎች ጨምሮ በዞኑ 8431 የሲቪ/ሰር/ሠራተኞች የሚገኙ ሲሆን ወ = 6172 ፣ ሴ= 2259 ሲሆኑ ይህም በፐርሰንት ሲሠላ 26.8% ሴቶች፣ 73.2% ወንዶች መሆናቸው በተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ ይታወሣል ፡፡

በዚሁ መሠረት በዞን ደረጃ ቀደም ሲል የመሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ለውጥ ሙሉ ትግበራ ውስጥ ቀደም ሲል ከገቡት ከ7ቱ ሴክተሮች ውስጥ ዝቅተኛ የሰው ኃይል 47.2% የሆነው ንግድ ኢንዱስትሪ መምሪያ ሲሆን፣ ከፍተኛ 81.1% የዞኑ ፋይ/ኢኮ/ል/መምሪያ መሆኑ ታውቋል፡፡ ወረዳዎችንም በሚመለከት ሳይለም በ26.7% ላይ ሲገኝ፣ ጊምቦ በ50.3% ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በዞኑ ውሰጥ በሚገኙ በሁሉም ሴክተሮች /በዞን፣በወረዳ/ አጠቃላይ የ6 ወር የሰው ኃይል መረጃ ለማሰባሰብ ተገቢ ፎርማት ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ሲሆን ከወረዳዎች የሚፈለግ መረጃ ተሟልቶ ባይቀርብም በዞን ደረጃ በሚገኝ መምሪያዎችና ጽ/ቤት የሚፈለግ የሰው ኃይል መረጃ በተሟላ ሁኔታ ለመሰብሰብ ተችሎአል ፡፡ ዝርዝር መግለጫም ከዚህ ጋር ተያይዞአል ፡፡

## በሰው ኃብት አስተዳደር የስራ ሂደት የተከናወኑ

በአንደኛ ዙር BPR ውስጥ ከገቡ 7 ሴክተሮች በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት ምደባ ለተሰጣቸው ሠራተኞች በምደባ ዙሪያ ወረዳዎች በደንብና መመሪያው መሠረት ምደባ እንዲካሄድ የተለያዩ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ በመመሪያው መሠረት እንዲሰሩ ተደርጓል ፡፡

- በአንደኛ ዙር ወደ BPR ለገቡ ሴክተር መ/ቤቶች ዝርዝር ተልኳል በየመምሪያዎች በወጣው መዋቅር መሠረት ምደባ ያላገኙትን ተንሣፋፊ ለሆኑ ሠራተኞች ከየመምሪያዎች ለዞኑ አቅም ግንባታ ምደባ እንዲያገኙ የተላኩ የመንግሥት ሠራተኞች በትምህርት ዝግጅታቸውና በአገልግሎታቸው እንዲሁም በሞያ መስመራቸው በመለየት በዞኑ እስትሪንግ ኮሚቴ ወደ ተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲመደብ ተደርጓል ፡፡
- በሁለተኛው ዙር BPR የገቡ መምሪያዎች በደንብ ቁጥር 72/2002 መሠረት በክልል አቅም ግንባታ የተለያዩ ሴርኩላሮች በተላለፈ መሠረት በተዋረድ ለመምሪያዎችና ለወረዳዎች በመላክ በመመሪያው መሠረት ሠራተኞች ምደባ እንዲገኙ ተደርጓል ፡፡
- በተጨማሪ በደንብ ቁጥር 72/2002 መሠረት ምደባ ያላገኙ ሠራተኞች በዞንና በወረዳ እስትሪንግ ኮሚቴ ምደባ በመሰጠት ላይ ይገኛል ፡፡
- ወረዳዎችን ድጋፍና ክትትል ከማድረግ አኳያ በወረዳዎች የሥራ ሂደቱ የገጠመውን የአሰራር ግድፍቶች ወደ ወረዳ በመውርድ ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡ ከጨና፣ከጠሎ ወረዳ እንዲሁም ከቢጣ ወረዳ የኢንፎርሚሽን ኮሙኒክሽን ሠራተኞችን ቅጥር እንዲፈፀም በተሰጠን ውክልና መሠረት ቅጥር ፈፀመናል ፡፡

## በሰው ኃብት ልማት የስራ ሂደት የተከናወኑ

ከዞንና ከወረዳ ስልጠና ነክ ጉዳዮች በተነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል ፡ ፡ከሲቭል ሰርቪስ ኮሌጅ በተላከ የረጅም ግዜ የርቀት ትምህርት በግላቸው ለመማር በተጠየቀው መስፈርት ከተወዳደሩት ውስጥ ወንድ 9 ሴት 1 በድምሩ 10 ሰራተኞች አሟልተው ስለተገኙ ትምህርት እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

ከክልል በተላከ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መሰረት ለዞናችን በተሰጠው ኮታ መሰረት የ2 ሰራተኞች መረጃ ለክልል ተላልፏል፡፡

ከክልሉ በተላለፈው ስለ ቀበሌ ስራ አስኪያጆች አዲስ መመሪያ ላይ በዞናችን ውስጥ ከሚገኙ 289 የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ለ 256 የቀበሌ ስራአስኪያጆች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በመጀመሪያ ዙርና በሁለተኛ ዙር ወደ ቢ ፒ አር ወደ ሙሉ ትግበራ በገቡ በሁሉም ሴክተሮች ውስጥ 715ቱ ስልጠና ወስደው ወደትግበራ ሲገቡ 865ቱ ደግሞ ስልጠና ያልወሰዱ ሰራቶች መረጃ ተጠናቅሮ በሚሰሩበት የስራ ሂደት ላይ ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ በመመቻቸት ላይ ይገኛል፡፡

## በኢኮቴ የስራ ሂደት ስር የተከናወኑ

በኢኮቴ የስራ ሂደት በግማሽ አመቱ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለዉ ተገልጸዋል

በዞንና በወረዳ በመንግስት መ/ቤቶች ዉስጥ ያሉ የኤሌክትሮኒክስ መገልገያ እቃዎች

ኮመፒዩተር 129 ፕሪንተር 118 ፎቶኮፒ 40 ፋክስ9

እስካነር 10

### አገልግሎት የሚሰጡ

ኮመፒዩተር 109 ፕሪንተር 110 ፎቶኮፒ 17 ፋክስ6

እስካነር 10

### አገልግሎት የማይሰጡ

ኮመፒዩተር 20 ፕሪንተር 8 ፎቶኮፒ 23 ፋክስ 3

እስካነር 0

መረጃዎች ለክልሉ ኢኮቴ የስራ ሂደት መላካችን ይታወቃል እንዲሁም በዞንና በወረዳ ዉስጥ ያሉ የገመድ አልባ ስልኮች የሚሰሩና የማይሰሩ ተለይተዉ በተመሳሳይ ሁኔታ ለክልል ተልኳል

በዞንና በወረዳ ዉስጥ የሚገኙ የገመድ አልባ ስልኮች እንደሚከተለዉ ይሆናል

አጠቃላይ በዞን 315 ቀበሌዎች ሲኖሩ 297ቱ የገጠር ቀበሌ 6ቱ አርብቶ አደር ቀበሌ ሲሆን 15ቱ ደግሞ የከተማ ቀበሌዎች ናቸዉ ከእነዚህ ዉስጥ 191 ቀበሌዎች የገመድ አልባ ስልኮች ያሏቸዉ ሲሆን የተቀሩት 112 ቀበሌዎች የገመድ አልባ ስልክ ያልገባላቸዉ መሆኑ የተሰበሰበዉ መረጃ ያመለክታል፡፡

በዞንና በወረዳ ዉስጥ በኢኮቴ ባለሙያዎች በየሴክተር መስሪያ ቤቶች ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል ከነዚህም ዉስጥ ለመጥቀስ ያክል በቦንጋ ፣ በአዲዮ ፣በጠሎ፣ በጨታ እንዲሁም በተለያዩ ወረዳዎች ተመሳሳይ ድጋፋዊ ክትትል በኢኮቴ ባለሙያዎች ተደርጓል፡፡ በቦንጋ ከተማ ለሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የአጭር ጊዜ መሠረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ 15 ሴቶችና 30 ወንዶች ሲሆኑ በድምሩ 45 ሰዎች በቦንጋ ከተማ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

በተጨማሪም በዞንና በወረዳ ደረጃ በአቅም ግንባታም ይሁን በተለያዩ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች የሚሰጡ ስልጠናዎች በአብዛኛዉ በኤሌክትሮኒክስ ማለትም በፕሮጀክተር በፕላዝማ በኮምፒዩተር የተደገፉ እንዲሆኑ የስራ ሂደቱ እየተገኘ አስፈላጊዉን እገዛ አድርጓል ፡፡

በዞንና በወረዳ ዉስጥ የተበላሹ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ተጠግነዉ ስራ እንዲሰሩ እየተደረገ ሲሆን ለመጥቀስ ያክል በመምሪያዉ ያለዉ ሁለት አመት በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየ ኮምፒዩተር በስራ ሂደቱ ተጠግኖ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል በተጨማሪም በመምሪያዉ ያሉ በቫይረስና በተለያየ ችግር ስራ ያቆሙ ኮምፒዩተሮች አስፈላጊዉ ጥገና ተደርጎላቸዉ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

## በስርአተ ፆታና ኤች አይቪ ኤድስ ሚኒስትሪሚንግ ዙሪያ

የ2002 ዓ.ም ከመ/ቤቱ የስራ ማስኬጃ ባጀት 2% ተመድቦ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ አየተሰራበት ይገኛል ፡፡

በኤች አይቪ ኤድስ የተጠቁ ወገኖችን ለመደገፍና ለማቋቋም ከሚደረገው ጥረት አኳያ በሴክተሩ ከዞን እስከ ወረዳ ከሰራተኞች የወር ደመወዝ 0.5% ተቆራጭ ሆኖ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

## II. የመልካም አስተዳዳር ፖኬጅ ትግበራን በተመለከተ

በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ለሀገራችን ህልውና ወሣኝ ጉዳይ ነው ሕዝቡ አምኖ ብቻ እንዲሰራ ማድረግ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ፈጣንና ተገቢ ምላሽ መስጠት አሠራሮችን ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ማድረግ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነት ፡-ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራር ማበጀት የመልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተከናወኑ አበይት ተግባራት ናቸው ፡፡

በመልካም አስተዳደር በኩል ለቀበሌዎች የተጠናከረ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ ጠሎ አዲዮ ፣ጨታና ቢጣ ወደፊት የወጡ ገዋታ፣ጊምቦ ፣ጨና ዴቻ በመሀል የሚገኙ ሴሆን ጌሻና ሣይለም አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ነው ፡፡

## 1. በጋራ መግባባትና በአሣታፊነት ዙሪያ

በመልካም አስተዳዳር ዙሪያ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን እስከ ቀበሌ ተፈፃሚነቱን ለማረጋገጥ ብሎም በየደረጃው ያሉ አካላት በየአከባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ እየተተገበረ ያለውን የመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ለመገምገም እና መሠረት ለማስያዝ እንዲረዳ ተሻሽሎ በተዘጋጀው የሱፐርቪዥን እና የኢንስፔክሽን አሠራር ማንዋል መሠረት ኮሚቴ የመመስረት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ሕዝቡ በግልና በጋራ የሚያከናውናቸውን ተግባራት አምኖ ብቻ እንዲያከናውን የማድረጉ ልምድ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በአብዛኛዎቹ ቀበሌዎች የምንጭ ጠረጋ የእግር መንገድ ሥራ የድልድይ ሥራ የት/ቤት ጥገና ወዘተ በሕዝብ ሙሉ ተሣትፎ የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ በሣይለም ወረዳ ሚሶ ቀበሌና በአዲዩ ወረዳ ቦቃ ቀበሌ የኀ/ሰቡን ጤንነት ለመጠበቅ በመንገድ ዳር በሕዝብ ተሣትፎ የተሰሩ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል ፡፡ ሕዝቡን አሣምኖ ወደ ልማት እንቅስቃሴ ለማስገባት በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን በጠሎ ወረዳ 5 ቀበሌዎች አዲዮ ወረዳ 9 ቀበሌዎች ጨታ ወረዳ 3 ቀበሌዎች ቢጣ ወረዳ 3 ቀበሌዎች ወደ ፊት የወጡ ሞዴል መሆናቸው ተለይቷል ፡፡ የጨታ ወረዳ ወደፊት ለወጡት ሶስት ቀበሌዎች የማበረታቻ ሽልማት የሰጠ መሆኑ ስረጋገጥ የሌሎቹ ወረዳዎች መረጃ አልደረሰንም ፡፡

የሞዴል ቀበሌዎች ዝርዝር

| ተ/ቁ | ወረዳ | ሞዴል ቀበሌ ብዛት | ሞዴል ቀበሌ ዝርዝር |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲዮ | 9 | ያጫ አንግቶ ቆላ ዩሚያ ሮሻ ቆጪጡ ግንዳቻ ሜሪ ወላ ሽራዳ |
| 2 | ጠሎ | 5 | ኦሚ ጋበላ ጩሪ አቺኒ አጢ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | ጨታ | 3 | ሻካ ኮራ ወርጣ |
| 4 | ቢጣ | 3 | አግዳኪቲ ወሽሮ አንድራቻ |

ሞዴል ቀበሌዎች ለመምረጥ በፖኬጅ የተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት የተደረጉ ቢሆንም ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ማለትም ከግብርናና ገጠር ልማት ከትምህርት ከጤና እና ከፍትሕ ሴክተሮች ጋር ተቀናጅቶ ከመስራት አንፃር ክፍተቶች ታይተዋል ፡፡

## 2. ቶሎ ምላሽ መስጠት

በሕዝብና መንግሥት መካከል የተጠናከረ ትስስር በመፍጠር ፈጣን ልማት ለማስመዝገብ የሕዝብ የጋራና የግል ጥያቄዎች ቶሎ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ነው ፡፡ በዚህ መሠረት ባለጉዳይን በቀጠሮ ማመላለስ በእጅጉ የቀነሰ ሲሆን የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በሥራ ስዓታቸው ቢሮአቸው በመገኘት ባለጉዳዩችን በማስተናገድ ላይ ይገኛሉ የሕዝብ ቅሬታ የሚስተናገድባቸው ሥርዓቶች በየቀበሌው የተዘረጋ ሲሆን ለጉዳይና ቅሬታ ማቅረቢያ ቅፃ ቅጾችን አዘጋጅተው የሚጠቀሙ ቀበሌዎች ቁጥር እየተበራከተ መጥቷል ፡፡ ለምሣሌ የጠሎ ወረዳ ለቀበሌዎች ቅፃ ቅጾች አዘጋጅቶ መላኩን አረጋግጧል ፡፡

## 3/ የግልፅነትና ተጠያቂነት አሠራር

በመንግሥት የሚወጡ መመሪያዎች ውሣኔዎች በየደረጃው የሚታቀዱ እቅዶችና አፈፃፀሙ ለሕዝብ ውይይት ቀርበው ግልፅ መሆን ይገባቸዋል ፡፡ በዚህም መሠረት ሕዝቡ የዕቅድ አፈፃፀሞችን በምክር ቤት ጉባኤዎች አማካይነት እንዲተችባቸው እየተደረገ ይገኛል ፡፡ በቀበሌ ደረጃ ሕዝቡ በፍጥነት መረጃ እንድያገኝ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን እንደመረጃ ዴስክ ለመጠቀም ተችሏል ፡፡

## 4/ ፍትሀዊነትና የሕግ የበላይነት

ኅብረተሰቡ የህግ የበላይነትን እያወቀ መብቱ እንዲጠበቅለት እያደረገና ግዴታውን እየተወጣ ከሄደ በልማትና በመልካም አስተዳዳር ሥራዎች ላይ ተሣትፎው እየጨመረ እንደምሄድ እሙን ነው ፡፡ በዚህም የሕዝቡን ንቃት ሕግ ከፍ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል ፡፡ ለአብነት በጨታና በሣይለም ወረዳ ፍ/ቤቶች ባለጉዳዩች አገልግሎት እስኪያገኙ ድረስ ተከታታይነት ያለው የንቃት ሕግ ትምህርት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ፡፡

በሁሉም ቀበሌዎች የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች በመኖራቸው ኅ/ሰቡ ወደ መደበኛ ፍ/ቤቶች በመመላለስ የሚያጠፋው ጊዜና የሚፈጠረው የሥራ ጫና ቀንሷል ፡፡

## 5/ ቀልጣፋነትና ውጤታማነት

ሁሉም ሴክተሮች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡ በመሆናቸው የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሎ ይገኛሉ ፡፡ የሚሰጠው አገልግሎት የበለጠ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆንና የተቀመጠውን ስታንዳርድ የጠበቀ እንዲሆን ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል ፡፡

በዞኑ ውስጥ አብዛኛዎቹ ቀበሌዎች ባለ ጉዳይ ማመልከቻ መፃፍ ሣያስፈልገው በተዘጋጀው ቅጽ ላይ በመሙላት አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል ፡፡

## 6/ የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ እንቅስቃሴን በተመለከተ

በዞናችን ውስጥ ከሚገኙት 289 የገጠር ቀበሌወች ውስጥ 269 ቀበሌዎች የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ተቀጥሮላቸው የቀበሌውን የዕለት ተዕለት ተግባራትን በማንቀሣቀስ መረጃ በማደራጀትና በማሰራጨት ባለጉዳይ በመቀበልና ለሚመለከተው ክፍል በማቅረብ ከቀበሌ መንግስት ተቋማት ጋር ማለትም

ከት/ቤቶች ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች የአንድ ወር ሥራ የቆዩበት መረጃ በመስጠትም ጭምር በመንቀሣቀስ ላይ ይገኛሉ ፡፡

በዴቻ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ 6 የአርብቶ አደር ቀበሌዎች የአርብቶ አደር አከባቢዎች ፖኬጅ ጥናት ከክልል ተጠናቆ ባለመድረሱ እንቅስቃሴ ማድረግ የተቻለ ባለመሆኑ ሕዝቡ በባህላዊ ጉሣ መሪዎቹ በኩል ችግሮቹን እየፈታ ይገኛል፡፡

## III. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም

የዞናችንን የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ስኬታማና ውጤታማ ለማድረግ አዲሱን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችላቸው ድጋፋዊ ክትትል እየተደረገ ይገኛል ፡፡

በአርብቶ አደር አካባቢ የሚታየውን የፍትሕ ችግር ለመቅረፍ ያመች ዘንድ የአከባቢውን 5 ልጆች በመመልመል በሕግ ሙያ በዲኘሎማ ደረጃ እየሰለጠኑ ይገኛሉ ፡፡

## የፖሊስ ሥርዓት ማሻሻያ ንዐስ ኘሮግራም

በየቀበሌው ሰላምና ፀጥታን በማስፈን ሕዝቡ በአንድ ልብ ወደ ፈጣን ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንዲዞር ለማድረግ መላውን ኀብረተሰብ ያሣተፈ የወንጀል መከላከል ሥራ/ኮሚንቲ ፖሊስንግ/አማራጭ የሌለው አደረጃጀት ነው ፡፡ በዚህ መነሻነት በዞናችን በሁሉም የአርሶ አደር ቀበሌዎች የተለያዩ የኀብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም ገበሬዎችን መ/ራንን ባለሀብቶችን ተማሪዎችን የሀይማኖት መሪዎችን ያሣተፈ የኮሚንቲ ፖሊስንግ ኮሚቴ ተደራጅቷል በተደረገውም እንቅስቃሴ የሥርቆት የዘረፋ የደን ጭፍጨፋ ወ.ዘ.ተ ወንጀሎች እየቀነሱ ሲሆን

ለአብነት በጌሻ ወረዳ የተሰረቁ የቤት እንስሣትን በአደረጃጀቱ መሠረት ለባለቤቶቻቸው ለማስመለስ ተችሏል ፡፡ በአዲዮ ፣በጠሎ ፣በጨታ በቢጣና በጌሻ ወረዳዎች የሥጋት ቀጠናዎች ተለይተው በልዩ ሁኔታ በኅብረተሰቡ ተሣትፎ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሲሆን በሁሉም ወረዳዎች ከአጐራባች አካባቢዎች ጋር ውይይት እየተደረገ ይገኛል ፡፡ በወንጀል መከላከል ዙሪያ ለ45868 የኅ/ሰብ ክፍሎች ሥልጠና ተሰጥቷል ፡፡

## የፍርድ ቤቶች ሥርዓተ ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም

የፍርድ ሂደትን ለማቀላጠፍ ማስረጃ በቅርብ በሚገኝባቸው ሁኔታዎች በአንድ ቀን ቃል ተቀብሎ የመወሰን ሁኔታ እየታየ መጥቷል ፡፡ ቀደም ሲል ይግባኝን ገልብጦ ለመስጠት ይፈጅ የነበረው ረዥም ጊዜ በፎቶ ኮፒ ማሽን በመታገዝ በትንሽ ደቂቃ ለማስተናገድ ተችሏል ፡፡

የማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች በየቀበሌው መጠናከር ኅ/ሰቡ ከልማቱ ሣይስተጓጐል ጉዳዩችን በአከባቢው እንዲፈታ የረዳ ሲሆን ትናንሽ ጉዳዩች በመያዝ በመጀመሪያ ፍ/ቤቶች ላይ ያስከትል የነበረውን የመዝገብ መጨናነቅ እንዲቀንስ አድርጓል ፡፡

በአሥሩም ወረዳዎች ሁለት ሁለት የመጀመሪያ ደረጃ ተዘዋዋሪ ፍ/ቤቶች በ20 ቀበሌዎች የተከፈቱ ቢሆንም አብዛኛዎቹ በበጀትና ሰው ሃይል እጥረት እንቅስቃሴ እንደማያደርጉ ተረጋግጧል ፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሁለት ወረዳ ላይ የተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል ፡፡

## IV. የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም

ኘሮግራሙ አዲስ ከመሆኑ አንፃር ሰፊ እንቅስቃሴ የተደረገበት ባይሆንም በቦንጋ ከተማ በማዘጋጃ ቤቱ በኩል ለኮብል ስቶን ሥራ የብር 300,000 ብር በጀት እንዲያዝ ድጋፍ የተሰጠ ሲሆን የብር 790000 ከክልሉ መንግስት የተላከውን በመጨመር የግማሽ ኪሎ ሜትር የዲንጋይ ንጣፍ መንገድ ለመስራት በታቀደው መሰረት እስካሁን ከ6400 ብር በላይ ወጭ ተደርጎ ከቦንጋ ቴክንክና ሙያ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ለ55 ወጣቶች ሥልጠና ተሰጥቶ ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ተሰጥቷል ፡፡

## ዋና ዋና ችግሮች

- **የሰው ኃይል ያለመሟላት** :- መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን በተሟላ መንገድ ለመተግበር አንዱና ዋነኛ የሰው ኃይል ነው ይሁን እንጂ በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች በዋናና ደጋፊ የሥራ ሂደቶች የሰው ኃይል የላቸውም በተለይ ለውጡን የሚመራና ድጋፋዊ ክትትል የሚያደርግ የለውጥ ኘ/ኘ/ጥ/ት ዋና የሥራ ሂደት የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ እንቅስቃሴ እንዲዳከም ትልቅ ምክንያት ሆኖአል ፤ይህ ችግር በሁሉም ወገኖች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሙያ መስመሩን ጠብቆ አቅምና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ሊመደብ ይገባል ፡፡
- **የቁሣቁስና በጀት እጥረት** :- ለሴክተር መ/ቤቶች ዓላማ መሳካት እነዚህ የተጠቀሱ ሁለት ነገሮች እጅግ ተፈላጊና ቁልፍ መሆናቸው የሚያጠያይቅ ባይሆንም እጥረቱ በወረዳዎች በግልፅ ይታያል ፡፡ በተፈለገው መንገድም ተሟልተው ያለመገኘታቸው በሥራው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሮአል ስለዚህ ይህን ውስን በጀት ሥራን ማዕከል ባደረገ መልክና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቅሞ አስፈላጊ የሆኑ ቁሣቁሶችን ደረጃ በደረጃ እያሟሉ መሄድና አጠቃቀሙም ጥንቃቂና ቁጠባ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ ነው በየወረዳው ተብላሽተው አገለግሎት የማይሰጡ የተክኖሎጂ

መሣሪያዎችም ተለይተው ጥገና በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል ፡፡

- **<u>የሥራ ቦታ ያለመመቻቸት</u>፡-** አዲሱን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለወጥን በመተግበር ለተገልጋዩ ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የቢሮ አደረጃጀት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው የሂደቱ አስተባበሪና ፈፃሚማዎች ባንድ ክፍል ውስጥ ሆነው አገልግሎት መስጠት ይገባቸዋል ይሁን እንጂ በወረዳዎች በፋይናንስ ሴክተር ካልሆነ በሰተቀር በሌሎች ሴክተሮች የቢሮ ችግር ጉልቶ ይታያል ፡፡ ይህ ጉዳይ እንደወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ከአስፈላጊነቱ አንፃር  እንዲስተካከልና ለሠራተኞች ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ብርቱ ጥረት ሊደረግ ይገባል ፡፡

- **<u>የአቅም ውስንነት</u> ፡-**በየሥራ ሂደቱ የተመደቡ ሠራተኞች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት ሥልጠና መውሰዳቸው ግልጽ ነው በሌላ በኩል ሥልጠና ሣያገኙ ተቀላቅለው  የሚሰሩ ሠራተኞች መኖራቸው የሚታወቅ ነው ፡፡ እንደሚታወቀው በመተግበር ላይ ያለነው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አዲስ እንደመሆኑ መጠን የሠራተኞቹም የአቀባበል ደረጃና አቅም የተለያየ ስለሆነ ተጨማሪ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል  ሥልጠና ሣያገኙ የተቀላቀሉም ተለይተው ሥልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል ፡፡

  ሠራተኞቹም ዕውቀታቸውንና ግንዛቤአቸው በየጊዜው ለማሣደግ ማኑዋሉን የዕለት ተዕለት መመሪያ አድረገው ሊያነቡ ይገባል ፡፡ ሠራተኞቹ የርስ በርስ ልምድና ተሞክሮ ልውዉጥ በማድረግ እንዲማማሩና አቅማቸውን እንድያሣድጉ የጐንዮሽ መደጋገፍ ሊበረታታ ይገባል ፡፡

- **<u>ድጋፋዊ ክትትሉ ደካማ መሆን</u> ፡-** በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች ማኑዋሉ በሚያዘው መሠረት ለየሥራ ሂደት ባለሙያዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይገባቸዋል ኃላፊዎቹ የሥራ መብዛት የሚታይባቸው ቢሆንም አዲሱ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ለየትኛውም ሥራችን ድጋፍ አቅም ስለሆነ ኘሮግራም በማውጣት የሥራ ሂደቶቹን ሊደግፉና ሊከታተሉ ይገባል፡፡

ተጓዳኝ ሥራዎችንም ከዚህ ጋር ከማስተሣሣር የሚፈፅመብት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርባቸዋል ለውጡ በባለቤትነት በኃላፍዎች ሊመራና እያንዳንዱ ተግባርም በዚህ ቅኝት ተደግፎ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

አልፎ አልፎ በባለሙያዎች አካባቢ የሚታየው የአመለካከትና የተቀላቀለ አስተሳሰብ ሊቀርፍና ሊጠራ የሚችለው ኃላፊዎች በሚያደርጉት ክትትልና የአስተሳሰብ ትግል ነው በBPR አተገባበር ዙሪያ የታዩትንና የሚታዩትን ችግሮች በየደረጃው እየተፈቱ እንዲሄዱ ለማስቻል ኃላፊዎች ወሣኝ ሚና አላቸው በድጋፋዊ ክትትሉ ወቅት ከአብዛኞቹ ሠራተኞች የሚቀርበው ቅሬታ ኃላፊዎች አይከታተሉንም አይደግፉንም የሚልነው ስለዚህ ኃላፊዎች ቁርጠኛ ሆነው ማኑዋሉ በሚጠይቀው መሠረት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እስከታች ድረስ በየወቅቱ በማድረግ ሴክተሮችንና የሥራ ሂደቶቹን ማብቃት ይኖርባቸዋል ፡፡

- **<u>የመረጃዎች አያያዝ ደካማ መሆን</u>**፡- ለየትኛውም ተግባር መረጃ ትልቅ ሀብትና መሠረት መሆኑ ይታወቃል ፡፡ በየወረዳው ያለው የመረጃ አያያዝ እጅጉን ደካማና ኃላቀር ነው ፡፡ ለዚህ ችግር ሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች ትልቅ ትኩረት ስጥተውበት ጉድለቱን በመፈተሽ ሊያስተካክሉና የማናከሪያ ሥራ ሊሠሩ ይገባል ይህ የሥራ መደብ ክፍት በሆነበት የሰው ኃይል የግድ መመደብ ይኖርበታል በመደቡ ያሉ ባለሙያዎችም ቢሆኑ በሥልጠና ታግዘው የመፈፀም አቅማቸውን በማጐልበት የተደራጀና የተስተካከለ ሥራ ሊሰሩ ይገባል ሌሎቹም ቢሆኑ የመረጃው ጥንቅር ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ተግባር ስለሆነ ተገቢውን ድጋፍና እገዛ መስጠት ይኖርባቸዋል ፡፡

- **<u>የተጠናከረ የሕዝብ ግኑኙነት ሥራ ያለመሥራት</u>** ፡- እያንዳንዱ ሴክተር መ/ቤትና የሥራ ሂደት የሚሰጠውን አገልግሎት ለተጠቃሚውና ለተገልጋዩ ኅብረተሰብ ግልፅና ግልፅ በሆነ መንገድ ማሣወቅ አለበት፡፡ አገልግሎትን ለማሣወቅ በተለያዩ መንገዶች መጠቀም ይቻላል **ለምሣሌ፡-** በብሮሸር በመጽሔት በማውያየት ግድግዳ/ማስታወቂያ ሠሌዳ በመጠቀም በሚዲያ በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡ ተገልጋዩም አገልግሎቱን ለማግኘት ይዞ መምጣት የሚገባው ነገር በቅድሚያ እንዲያውቅ ተደርጐ ተዘጋጅቶ እንዲመጣ መደረግ ይኖርበታል፡፡

  በሌላ በኩል ተገልጋዬ ሕብረተሰብ ቅሬታውንና አስተያየቱን በነፃ መግለጽ የሚችልበትን ሥርዓት በመዘርጋት ምላሹን በወቅቱ የሚያገኝበትን አሠራር ማጐልበት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ አሠራራችንን ለተገልጋዩ ኀብረተሰብ ግልፅ ማድረግ ይኖርበናል፡ ፡ ኀብረተሰብ በቂ ግንዛቤ ጨብጦ ተጠቃሚነቱን እንዲያረጋግጥና ከሱ የማጠበቀውን ድጋፍና ግዴታ እንዲያሟላ በቂና የተሟላ የሕዝብ ግኑኝነት ሥራ ሊሠራ ይገባል ፡፡ እያንዳንዱ የኀብረተሰብ ክፍል የፈለገውን አስተያየት አለ የሚለውን ቅሬታ ሣይሸማቀቅ በነፃነት እንዲያቀርብ ማበረታታት ያስፈልጋል ፡፡ የሚቀርበው አስተያየት ለተቋሙ ትልቅ ግብዓት ስለሆነ ሊበረታታ ይገባል፡፡